በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

በደብረ ነጎድጓድ ቅዱስ ዮሐንስ ወመካነ ጎልጎታ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን

የፍቁረ እግዚእ ሰንበት ት/ቤት ሕፃናት ክፍል

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መግቢያ ትምህርት - መጣሪያ ለ2014 ዓ.ም የ8ኛ እና 9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ

ግንቦት 2014 ዓ.ም

(ሙሉ በሙሉ ከሰንበት ት/ቤቱ የውጣት ትምህርት ክፍል የተወሰደ)!





ማውጫ

- መግቢያ
- የጥናቱ አላማ
- ምዕራፍ አንድ
  - የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መግቢያ
- ምዕራፍ ሁለት
  - የመጽሐፍ ቅዱስ ባህል
- ምዕራፍ ሦስት
  - የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም

መግቢያ

ይህንን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠረ እግዚአብሔር አምላክ ነው ።የሰው ልጆች ሁሉ አምላካቸውን ያምናሉ ትዕዛዙን ይጠብቃሉ ።እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተናገረው ደግሞ የምናገኘው በመጽሐፍ ቅዱስ ነው ስለዚህ ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈቃዱን ለማወቅ ትዕዛዛቱን ለመጠበቅ ከመንገዱ ላለመውጣት መጽሐፍ ቅዱስን ልናነብና እንደፍቃዱ ልንኳዝ ያስፈልጋል ።መጽሐፍ ቅዱስን ደግሞ እንዲሁ ዝምብለን አናነበውም የራሱ የሆነ የአነባበብ ስርዓት የአፃፃፍ ባህል የሚተረጎምበት መንገድ አለው ይህንን ደግሞ መፅሐፍ ቅዱስን በማጥናት ልንመልሰው ያስፈልጋል ቅዱስ የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል አሁን ያለበት ደረጃ እንዴት እንደደረሰ ማወቅ ተገቢ ነው

የጥናቱ ዓላማ

- መጽሐፍ ቅዱስ መቼ፣የትና እንዴት በማን እንደተጻፈና በውስጡ ምን ነንደሚገኝ ማወቅ
- መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ሁኔታና የአተረጓጎም ስልት ማወቅ
- የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥር በማንና መቼና የት እንደተወሰነ ማወቅ
- በተማርነው ትምህርት ይበልጡኑ ወደ ደግዚአብሔር መቅረብ
- በመጽሐፍ ቅዱስ ዙሪያ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ መስጠት

መጽሐፍ ቅዱስ ማለት ምን ማለት ነው

ከሁለት ጥምር ቃል የተገኘ ሲሆን ***መጽሐፍ*** ማለት በአንድ ጥራዝ ስር የተሰባሰቡ ጽሑፎች ማለት ሲሆን ***ቅዱስ*** ማለት ደግሞ የተለየ የተመረጠ ማለት ነው ።በአጠቃላይ ***መጽሐፍ ቅዱስ*** ማለት በአንድ ጥራዝ ስር የተሰበሰቡ የተለዩ የተመረጡ ጽሁፎች ማለት ነው ።

መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ቅዱስ ተባለ

1. አስገኚው እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ ነው 1ጴጥ 1 ፥ 15-16 ‹‹ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተም ደግሞ በኑሮቸው ሁሉ ቅዱስ ሁኑ ››
2. በእግዚአብሔር መንፈስ የተነሳሱ ቅዱሳን ሰዎች የጻፉት በመሆኑ ዘሌ 17 ፥ 14
3. ዘመን የማይሽረው ስለሆነ ማቴ 24 ፥ 23
4. በእድሜው 4014 -96 ዓ.ም ከመጽሐፈ ሄኖክ እስከ ዮሐንስ ራዕይ
5. የሰውልጅ ከመፈጠሩ በፊት ያለውን ነገር ብርግጠኝነት ስለሚናገር ዘፍ 1 ፥ 1 ‹‹እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይና ምድርን ፈጠረ ››

የቀጠለ...

6. ወደፊት ስለሚመጣው ነገር በእርግጠኝነት ስለሚናገር ኢሳ 7 ፥ 14
7. የትንቢት ዕውነታነት ስላለው ኢሳ 7 ፥ 14 ሚኪ 5 ፥ 2
8. የሚያምኑበትን የሚያነቡትን ወደ ቅድስና የሚያመራ የሚለውጥ ሃይል በመሆኑ ሮሜ 1፥ 16
9. ክብረ ቅዱሳንን ስለሚዘክር
10. በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉ ተአምራቶች በእኛም ህይወት በመፈጸማቸው

መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ይጠቅማል?

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅምን ዘርዝሮ መጨረስ አይቻልም ነገርግን ጥቂቶቹን ለብነት ያህል

1. የሰው ልጅ እንዲመራበት መዝ 118 ፥105 ‹‹ ህግ ለእግሬ መብረት ለመንገዴ ብርሃን ነው ››
2. ለምህንድስና ዘፍ 6 ፥ 14 -16

‹‹ በለአራት ማዕዘን የእንጨት መርከብ ለአንተ ስራ በመርከቢቱም ክፍሎችን አድርግ በውስጥም በውጭም በቅጥራን ለቅልቃት መርከቧም ውስጥ እንዲህ ታደረጋለህ የመርከቢቱንም ርዝመት 300ክንድ ወርዱንም 50 ክንድ ከፍታዋም 30 ክንድ ይሁን ለመርከቢቱም መስኮትን ታደርጋለህ ከቁመቷም ክንድ ሙሉ ትተህ ጨርሳት የመርከቢቱንም በር በጎኗ አድርግ ››

የቀጠለ …

3. ለህክምና ኩፋ 10፥ 7

‹‹ በምድር እንጨት ያድን ዘንድ ደዌአቸውን መድኀኒት ከማሳቻቸው ጋር ለኖኅ ነገርከው ኖኅም በመድኀኒቱ ዓይነት ሁሉ እንዳስተማርከው በመጽሐፍ ሁሉን ጻፈ ››

4. አስተዳደርና ዳኝነት ዘጸ 32፥ 32

‹‹ ይህንን ኃጥያታቸውን ይቅር በላቸው ያለዚያ ግን ከጻፍከው መጽሐፍ እባክህ ደምስሰኝ ››

5. ግብርና ዘዳ 23 ፥ 10

‹‹ ስድስት አመት ምድሪቱን ዝራ በሰባተኛው አመት ግን ተዋት አሳርፋትም ››

6. የእግዚአብሐርን ትዕዛዝና ፈቃድ ለማወቅ ዘዳ 4 ፥ 2

‹‹ እኔ ያዘዝኋችሁን የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ትጠብቃላችሁ እንጂ ባዘዝኋችሁ ቃል ላይ አትጨምሩም ከእርሱም አታጎድሉም ››

መጽሐፍ ቅዱስን የምናጠናበት ምክንያት

ሀ. የሀይማኖታችን መነሻና መድረሻ በመሆኑ ይሁ 1 ፥3 ዕብ 11 ፥ 1

ለ. በቃሉ ውተት ለማደግ ‹‹ ተንኮል እንደሌለባቸው አሁን ነንደተወለዱ ህጻናት የቃሉን ውተት ተመኙ ›› እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ

ሐ. የዲያብሎስን ሽንገላ እንድደቃወምበትበ ኤፌ 6 ፥ 10-17 ‹‹ ንግዲስ ወዲህ ብግዚአብሔር በኃይሉ ጽንአት በርቱ የሰይጣንን መቃወም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ጋሻ ልበሱ ሰልፋችሁ ከጨለማ ገዥዎች ጋራና ከሰማይ በታች ካሉ ከክፉዎች አጋንንት ጋር ነው እንጂ ከስጋዊና ከደማዊ ጋር አደለምና...ይኸውም የእግዚአብሔር ቃል ነው ››

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን ምን መሆን አለበት

1. ከሳይንሳዊ እይታ የጸዳ መሆን አለበት 1ቆሮ 2 ፥14 ፣2 ፥5 የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን በራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መሆን አለበት
2. ነገረ ድህነት ያማከለ መሆን አለበት
3. ትውፊታዊ መሆን አለበት
4. ነገረ ቅዱሳንን ያማከለ መሆን አለበት ዕብ 13 ፥7 ‹‹ የእግዚአብሔር ቃል የነገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ መልካሙን ጠባያቸውን አይታችሁ በእምነት ምሰሏቸው ››
5. ወደምስጠራተ ቤተ ክርስቲያን የሚያመራ መሆን አለበት

መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ የሚያስገኘው ጥቅም

1. ***<u>ያድናል</u>*** ዮሐ 5 ፥25 ‹‹ እውነት እውነት እላችኋለሁ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ቃል የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል እርሱም አሁን ነው ። የሚሰሙትም ይድናሉ ››
2. ***<u>ያስተምራል</u>*** መዝ 118፥ 33 ‹‹ አቤቱን የእውነትን መንገድ አስተምረኝ ሁልጊዜ እፈልጋታለሁ ››
3. ***<u>ይገስጻል</u>*** 2ጢሞ 3፥ 16 ‹‹ የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ስራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ … ይጠቅማል››
4. ***<u>ያረጋጋል ምሳ</u>*** 1፥ 3 ‹‹ የሚሰማኝ ግን በተስፋ ይኖራል ከክፉም ሁሉ ያለድንጋጤ ያርፋል

የቀጠለ...

5. ጥበብን ይሰጣል መዝ 18፥ 8 ‹‹ የእግዚአብሔር ምክር የታመነ ነው ህፃናትንም ጠቢባን ያደርጋል ››

6. ሀይወትን ይሰጣል ዮሐ 6፥ 63 ‹‹ እኔ የነገርኳችሁ ቃል መንፈስ ነው ህይወትም ነው ››

7. መድኃኒት ነው ያድናል ሐዋ 13፥ 26 ‹‹ እግአዚአብሔርን የምትፈሩ ሆይ ለእናንተ የዚህ የመዳደ ቃል ተላከ ››

8. ሰላምን ይሰጣል መዝ 118፥ 165 ‹‹ ሕግህን ለሚወዱ ብዙ ሰላም ነው እንቅፋትም የለባቸውም ››

መጽሐፍ ቅዱስ መቼ ተጻፈ

- የመጀመሪያው መጽሐፍ መጽሐፈ ሄኖክ ነው ይህ መጽሐፍ የተጻፈው 1486 ዓ.ዓ /4014 ቅ/ል ክርሰቶስ ሲሆን
- የመጨረሻው መጽሐፍ የዮሐንስ ራዕይ ሲሆን ይህ መጽሐፍ ደግሞ ከ96 – 98 ዓ.ም ተጽፏል ።

መጽሐፍ ቅዱስ የት ተጻፈ

ብሉይ ኪዳን

- መጽሐፈ ሄኖክ በደብረ ቅዱስ
- አስቴርና ዮዲት በፋርስ (ኢራን)
- ስምንቱ የመዝሙርና የጥበብ መፃሕፍታት በኢየሩሳሌም
- የሙሴ መጻሕፍት በሲና ምድረ በዳ (ሳውዲ አረቢያ)
- ት.ሀዝ፣ት.ዳን፣አስሩ ደቂቅ ነቢያት በባቢሎን (ኢራቅ)
- ሆሴዕና ሚልክያስ በኢየሩሳሌም
- መጽሐፈ ጦቢት በነነዌ
- መጽሐፈ ኢያሱ በከነዓን

የቀጠለ...

ሐዲስ ኪዳን

- ማቴዎስ ወንጌል በፍልስጤም
- ማርቆስ ወንጌል በሮም
- ሉቃስ ወንጌል በግሪክ
- የዮሐንስ መጻህፍታት በኤፌሶን ፣በፍጥሞ ደሴት
- የቅ/ጴጥሮስና የቅ/ጳውሎስ መፃሕፍት በአቴና ፣በሮም ፣በግብጽ ወዘተ...
- የያዕቆብ መልዕክት በኢየሩሳሌም

መጽሐፍ ቅዱስን ማን ጻፈው

መጽሐፍ ቅዱስን ከአርባ በላይ ቅዱሳን ሰዎች ከተለያያ ቦታ ተነስተው ጽፈውታል

- ከእረኝነት ሙሴ
- ከነገስታት ዳዊት ሰሎሞን
- ከካህናት ሕዝቅኤል
- ከተማሩት ሉቃስ
- ከአሣ አጥማጅነት ዮሐንስ፣ጴጥሮስ ፣
- ከቀረጮ ማቴዎስ

በምን ቋንቋ ተጻፈ

የብሉይ ኪዳን አብዛኛው መጻህፍታት በዕብራይስጥ

- ትንቢተ ዳንኤል በአረማይክ
- ማርቆስ ወንጌል በሮማይስጥ
- ማቴዎስ ወንጌል በዕብራይጥ

የመጽሐፍ ቅዱስ ዝግጅት

1. ቅዱስ መጽሐፍን ያሰባሰበው መንፈስ ቅዱስ ነው ኢሳ 34 ፥16 ‹‹ ‹‹እግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም አፉ አዝዞአልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም››

የተለያዩ አባቶች ያሰባሰቡ ሲሆን ካህኑ ዕዝራ ፣ማሶራውያን ፣70ው ሊቃናት ብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን አሰባስበዋል የሐዲስ ኪዳንን መፃሕፍት ጨምረው ደግሞ 81 እንደሆነ ወስነውልን ሐዋርያት አባቶቻችንን አሰባስበዋል

2. መዘጋጀት

ማሶራውያን አናባቢዎችን በመጨመር የቋንቋ ምልክት በመጨመር

አሞንዮስና አውሳብዮስ በክፍል በክፍል በማዘጋጀት

ስቴቨን ላንግተን በ1228ዓ.ም በምዕራፍ

ሮበርት ስቲን በ1551ዓ.ም በቁጥር

የቀጠለ

3. አሰያየም
1. በጸሐፊያቸው ስም -መጽሐፈ ሄኖክ
2. በይዘታቸው -ዘፍጥረት
3. በፀሐፊያቸውና በይዘታቸው -መ.ዳዊት መኃልየ መኃልይ ዘሰለሎሞን
4. በባለ ታሪኩ ስም መ.አስቴር
5. በተላከላቸው ሰዎች ሀገር ስም -ወደ ሮሜ
6. በተላከላቸው ሰዎች ስም -ወደ ጢሞቴዎስ

መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ የሚደረግ ዝግጅት

- ሁለት አይነት ዝግጅት ማድረግ አለብን

ሀ. ውስጣዊ ዝግጅት

ለ.ውጫዊ ዝግጅት

ሀ.ውስጣዊ ዝግጅት

---ፍላጎት ሊኖረን የተረጋጋ መንፈስ ሊኖረን ያስፈልጋል

ምሳ 1፥ 33 ‹‹ የሚሰማ ግን በእርጋታ ይቀመጣል ››

---እራሳችንን ለቃሉ ልናዘጋጅ ያስፈልጋል

ሐዋ 16፥ 140 ‹‹እግዚአብሔር ልቦናዋን ከፍቶላት ነበርና ጳውሎስ የሚየስተምረውን ታደምጥ ነበረ ስሟም ልድያ ይባላል››

---ልቦናን ንጹህ ማድረግ ዮሐ 1፥ 48 ‹‹ተንኮል የሌለበት የእስራኤል ሰው ›› 1ጢሞ 1፥5 -7‹‹የትዕዛዝህ ፍጻሜ ግን ከንጹህ ልብና ከበጎ ህሊና ግብዝነትም ከሌለበት እምነት የሚወጣ ፍቅር ነው።።››

የቀጠለ …

ለ.ውጫዊ ዝግጅት

-->ከማንበባችን በፊት

* ማዘጋጀት

* በጸሎት መጀመር

-->በምንናብ ጊዜ

* መምረጥ ያስፈልጋል ቦታ፣ ጊዜ፣ ርዕስ

* ፈሪሃ እግዚአብሔርን ገንዘብ ማድረግ ዘፍ 18 ፥27 ‹‹እኔ አመድና አፈር ስሆን ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር ወሰንኩ ›› መዝ 21፥ 6 ‹‹እኔ ትል ነኝ ››

የቀጠለ...

* ከመረዳት ጋር ማንብ አለብን ማቴ 22፥29 ‹‹መጻህፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ››፣ ሆሴ 4፥5‹‹ህዝቤ እውቀትን ከማጣቱ የተነሳ ጠፋ››

* መምህራን አባቶቸን መጠየቅ ሉቃ2 ፥46‹‹በሊቃውንት መካከል ተቀምጦ ሲሰማቸውና ሲጠይቃቸው አገኙት››

* ማስታወሻ መያዝ አበው‹‹በቃል ያለ ይረሳል ...››

* በጸሎት መደምደም

ምዕራፍ ሁለት
የመጽሐፍ ቅዱስ ባህል

የመጽሐፍ ቅዱስ ባህል

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ለዓለም ሁሉ ህዝብ ነው ዓለም ደግሞ በውስጧ በተየያ መንገድ የሚኖሩ ሰዎች ያሉባት ናት መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ የራሱ የሆነ የአጻጻፍ ባህል ስርዓት አለው በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ለዓለም ህዝብ ቢሆንም አብዛኛውን ስርዓት የያዘው ግን የእስራኤላውያንን ባህል ነው ሰዎች ቀጥታ ወደራሳቸው በሚወስዱበት ወቅት ሲስቱና ለምንፍቅና መነሻ ሲሆኑ እንመለከታለን ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ የሌላውን ባህልና ስርዓት ቀጥታ ወደራሳቸው ስለሚያመጡት ነው። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን ለማወቅ ፣ ለመረዳት የዕብራውያንን ባህል ማጥናት አለበት ምክንያቱም በአንዱ ባህል ትክክል የሆነው ነገር በሌላው ስንመለከተው የተሳሳተ ሊሆን ስለሚችል ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስን ባህል ማጥናት ተገቢ ነው ።

መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት ስድስት ነገሮች ያስፈልጋሉ

1. መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበትን መልክዓ ምድር ማወቅ
2. መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበትን የሕዝቦቹን ታሪክ ማወቅ ያስፈልጋል
3. ለህዝቦቹን ባህል ማወቅ ያስፈልጋል
4. የእንስሳት ጥናት ያስፈልጋል
5. የእጽዋት ጥናት ያስፈልጋል
6. የማእድናት ጥናት ያስፈልጋል

፭ የእብራውያን ስም አወጣጥ

- ስም ጠባይን ፣ግብር፣ ሁኔታን ይገልጣል በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ምናገኛቸው ስሞች ከመጠሪያነት በተጨማሪም በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ይገልጣል

ሀ . ለሰዎች የሚሰጥ ስያሜ ምሳሌ ሴት ምትክ

ለ ለቦታዎች የሚሰጥ ስያሜ ምሳሌ መሪባ ጠብ ክርክር

ሐ. ለሰዎች የሚሠጥ ቅጽል ስም

በሶሥት መንገድ ይሰጣል

1. በግብራቸው ---መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ
2. በትውልድ ቦታቸው --- መግላዊት ማርያም
3. በቤተሰብ ስም --- ኢያሱ ወልደ ነዌ

፪ .የአነጋገር ዘይቤ

1.1. በማራቅ መናገር ኢያ 5 ፥1 4 ‹‹ጌታዬ ለባሪያው የሚነግረው ምንድነው ››

ማቴ 16 ፥ 13 ‹‹ሰዎች የሰውን ልጅ ማን ይሉታል ››

1.2. ደጊሞተ ቃል (ቃልን መድገም) ዮሐ 3 ፥3-5 ‹‹እውንት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልከተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ ዘንድ አይችችም ››

መዝ 21 ፥10 ‹‹አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ››

የቀጠለ....

1.3. ከአንተ/ከአንቺ ጋር ምን አለኝ

+1ነገ 17 ፥18‹‹የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከአንተ ጋር ምን አለኝ ኃጥያቴንስ ታስብ ዘንድ ልጄንስ ትገልብኝ ዘንድ ወደእኔ መጥተሀልን አለችው>>

+2ነገ 3 ፥13‹‹ኤልሳዕም የእስራኤል ንጉስ እኔ ከአንተ ጋር ምን አለኝ ››

+ማር 5 ፥7 ‹‹የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ እኔ ከአንተ ጋር ምን አለኝ እንዳታሰቃየኝ በእግዚአብሔር እለምንሀለሁ››

+2ሳሙ 16 ፥9-12‹‹.....እናንተ የጽሩያ ልጆች ሆይ እኔ ከእናንተ ጋር ምን አለኝእግዚአብሔር ዳዊትን ስደብው ብሎ አዝዞታልን ይርገመኝ ለምንስ እንዲህ ታደርጋለህ የሚለው ማን ነው አለ....››

የቀጠለ….

- ዮሐ 2፥4‹‹የወይን ጠጅከ የላቸውም አለችው እርሱም አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ ጊዜዬ ገና አልደረሰም አላት እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምም የሚላችሁን አድርጉ አለቻቸው››
- አንቺ አላት አንተ/አንቺ እንደ እስራኤላውየን ባህል ክብር የመስጠት ንግግር ነው
- ሴት አላት
  1. አጥንትሽ ከአጥንቴ ሥጋሽ ከሥጋዬ ሲላት ነው
  2. ሴት ማለት ምትክ ማለት ነው:: ዘፍ 4፥25
  3. ፍፁም ሴት ሲላት
- ጊዜዬ ገና አልደረሰም አላት
  1. ይሁዳ ወጥቶ ነበርና
  2. በማድጋው የነበረው ወይን ተሟጦ አላለቀም ነበርና
  3. ድንግል ምድራዊውን ብቻ ሳይሆን ሰማያዊውንም ወይን ጠይቃ ነበረና

የቀጠለ.....

- በአጠቃላይ ፍቺው አንቺ አጥንትሽ ከአጥንቴ ሥጋሽ ከሥጋዬ የሆንሽ አንቺ ምትክ የሆንሽ አንቺ ፍፁም ሴት የሆንሽ እናቴ ሆይ ያልሺኝን እንዳላደርግ የሚከለክል ምን ጠብ አለኝ አደርግልሻለሁ ማለት ነው።ለዚህ ነው እናቱ ማርያም ከንግግሩ በኋላ የሚላችሁን አድርጉ ያለቻቸው በእናታችን ምልጃ የዶኪማስ ቤት

፫ስዕላዊ አገላለጽ

- ስዕላዊ አገላለጽ በአይነ ሥጋ የማይታዩ ነገሮችን በህሊና በሚረዱና ሊታዩ በሚችሉ ስዕላዊ አገላለጽ አጉልተው ይፅፋሉ
- ት.ኢሳ 6፥1-2‹‹እግዚአብሔርን ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር ሱራፌልም ከእርሱ ላይ ቆመው ነበር ለእያንዳንዳቸውም 6 ክንፍ ነበረው በሁለት ክንፉ ፊቱን ይሸፍን ነበር በሁለት ክንፉ እግሮቸሁን ይሸፍን ነበር በሁለት ክንፈሩ ይበር ነበር አንዱ ለአንዱ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተመልታለች እያለ ይጮህ ነበር ››
- መዝ 17፥2 ‹‹እግዚአብሔር አለቴ፣አምባዬ፣መድኃኒቴ፣አምላኬ በእርሱ የምታመንበት እረዳቴ፣መታመኛዬ የደህንነቴ ቀንድመጠጊያዬ ነው››

፬ እንቆቅልሽ

- እንቆቅልሽ ስለ አንድ ርዕሰ ጉዳይ በሌላ አስመስሎ መናገር ፣በስውር መናገር እንቆቅልሽ እንለዋለን።
- በ2ሳሙ 12፥1-6
- መሳ 14፥12-13‹‹ከበላተኛ አፍ ውስጥ መብል ወጣ ከብርቱውም ውስጥ ጥፍጥ ወጣ››

፭ ግነት

- በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰዎችን የሌሎች ነገሮችን ጠባይ፣ጉልበት፣ብዛት ወዘተ ለመግለፅ ሲፈለግ ተቀራራቢ በሆነ መልኩ ምሳሌ ተመስሎ ይነገራል
- ዘፍ 22፥17 ‹‹ ዘርህን እንደ ምድር አሸዋ እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛልሀለው››
- 1ነገ 1፥40 ‹‹ከጩኸታቸው የተነሳ ምድር ተናወጠች››
- ማቴ 23፥24 ‹‹ትንኝን የምታጠሩ ግመልን የምትውጡ››
- 1ነገ 1፥39 ‹‹ንጉስ ሺ አመት ንገሥ››

፮ ወንድም

- በመጽሐፍ ቅዱስ ባህል ወንድም ለመባል የግድ ከአንድ እናትና አባት መወለድ የለባቸውም በተለያየ ሁኔታ የሚቀራረቡ ሰዎች ወንድማማቾች

1. በሐገር ልጅነት ዘፀ 2፥12 ‹‹ሙሴ አደገ ወደ ወንድሞቹ ወጣ መከራቸውንም ተመለከተ የግብፅም ሰው ከወንድሙ ከእስራኤል ልጆች አንዱን ዕብራዊውን ሰው ሲመታ አየው
2. በአንድ ነገድ ልጅነት 2ሳሙ 19፥11‹‹ለይሁዳ ሽማግሌዎች እንዲህ ብላችሁ ንገሩአቸው የእስራኤል ሁሉ ነገር ወደ ንጉሱ ደርሷልና ንጉሱን ወደ እቤቱ ከመመለስ ለምን ዘገያችሁ እናንተ ወንድሞቼ የአጥንቴ ፍላጭና የስጋዬ ቁራሾች ናችሁ››

የቀጠለ…

3. በዝምድና ዘጎ 20፥14‹‹ወንድምህ እስራኤል እንዲህ ይላል



የቀጠለ…

4. በባልንጀርነት 2ሳሙ 1፥26‹‹ወንድሜ ዮናታን ሆይ እኔ ስለ አንተ እጨነቃለሁ››



የቀጠለ…

5. በቤተሰብ አባልነት ዘፍ 13 ፡8 ‹‹እኔና አንተ ወንድማማቾች ነንና በእኔ በአንተ በእረኞቻችን መካከል ጠብ እንዳይኖር እለምንሀለሁ››



የቀጠለ...

6 .በሃይማኖት አንድነት ፊል 1 ፥12 ‹‹ ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ይህ የደረሰብኝ በእውነት ወንጌልን ለማስፋፋት እንደሆነ ታወቁ ዘንድ››

ሐዋ12፥17 ‹‹ይህንን ለያዕቆብና ለወንድሞቼ ንገሩ››

የጌታ ወንድሞች

- ማር 6፥3‹‹ይሄ የፀራቢው የማርያም ልጅ የያዕቆብና የዮሳ የይሁዳም የስምኦንም ወንድም አይደለምን እህቶቹስ በዚህ በእኛ ዘንድ አይደሉምን ›››
- አባ ጄሮም 381 ለተነሳ ሄልቪድየስ ለተባለ ፀረ ማርያም መናፍቅ በሰጠው ምላሽ ወንድሞቹ የተባሉት የአክስቱ ልጆች ናቸው ብሎ መልሶለታል

የቀጠለ...

- ዮሐ 19፥25‹‹ነገር ግን በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱ የእናቱም እህት የቀለዮጳ ሚስት ማርያም ፣መግደላዊት ማርያም ነበረች››
- ማቴ27፥55-56‹‹ ኢየሱስን እያገለገሉ የተከተሉ ብዙ ሴቶች በሩቅ ሆነው ሲመለከቱ በዚያ ነበሩ ከእነርሱም መግደላዊት ማርያም ፣የያዕቆብና የዮሳ እናት ማርያም የዘብዴዎስ የልጆቹ እናት ነበሩ።››
- ይሁ 1 ‹‹የኢየሱስ ክርስቶስ ባርያ የያዕቆብ ወንድም ››

ምዕራፍ ሦስት
የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም

በቀጥታ የተወሰዱ ቃላት

- ኤልሻዳይ(ሁሉን የሚችል አምላክ)
- ያህዌ ይርኤ(እግዚአብሔር ያያል)
- መሪባ(ጠብ ክርክር)
- አዶናይ(ጌታ)
- ፀባኦት(የኃያላን ጌታ)
- ሃሌ ሉያ(እግዚአብሔርን አመስግኑ)

የመጀመርያው የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም

*ከእብራይስጥ ወደ ግዕዝ 980ቅ.ል.ደ

*ከእብራይስጥ ወደ ፅርህ 284ቅ.ል.ደ

*ኑንክለስ እና ዮናታን ወደ አረማይክ

*አባ ጀሮም 366 ዓ.ም ወደ ቩልጌት

*ቅሚስሮኝ እና ቅሳህክ ወደ አርመኒኛ

የቀጠለ...

*ማርቲን ሉተር 16መ/ክ/ዘ ወደ ጀርመኒኛ

*ቴንዳሌ 1525 የተወሰኑትን ወደ እንግሊዘኛ ሉተርን ተከትሎ የተረጎመ

*ኮፍርዳሌ 1936 የማቴዎስ መጽሐፍ ቅዱስ

*የጄኔቫ ፕሮቴስታንቶች The Geneva Bible

*ንጉስ ጀምስ 1604-1611 The King Jems version

*እንግሊዞች 1881-1885 The Rivasie version

የቀጠለ...

- እንግሊዝ 1885 The Rivasie version
- 1970 የእንግሊዝ ካቶሊኮች የአየር ላንድ ፕሮቴስታንትና ካቶሊኮች The New English Bible
- 1989 The Revaised English Bible
- 1901 The American stanedard version
- 1952 The Rivasied stanedard version
- The new American Bible
- 1976 Todays English Bible

ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ኢትዮጵያ

- የብሉይ ኪዳን ጊዜ
- 980 ቅ.ል.ክ በቀዳማመዊ ምኒልክ ዘመን
- በኢትዮጵያ ንጉሥ አይሹር በነገሠ ጊዜ ‹‹የእኛና የእናንተ አባቶች የፃፏቸው መጻሕፍት ተቃጠሉ ወይስ ድነዋል እናንተስ እንደምን አላችሁ ለጣኦት ትሰግዳላችሁን ሰንበትንስ ሻራችሁን ?››

- ከባቢሎን ምርኮ በሁኋላ በእስራኤል ላይ ዘሩባቤል በነገሠ ጊዜ ‹‹ሰላም ለአንተ ይሁንና ስለ እግዚአብሔር ብለህ የለመንኩህን ስማኝ ከኢየሩሳሌም ጥፋት አስቀድሞ ነቢያት የጻፏቸው መፃህፍት በአያትህ በሰሎሞን ልጅ በምኒልክ ዘመን መጥተው በሐገርህ አሉና ጽፈህ ላክልኝ ብዬ በአባቶችህ ፈጣሪ በከበረ ስሙ እማልድሀለው ::እኔም ወደ እናንተ ያልመጡትን በእኛ ዘንድ ያሉትን እልክልሃለው ይህ ለእኔም ለአንተም ጥሩ ነው ››

በሐዲስ ኪዳን

- በአባ ሰላማ ከሰቴ ብርሃን(ፍሬምናጦስ)4መ/ክ/ዘ
- ተሰዐቱ ቅዱሳን 5መ/ክ/ዘ
- አባ ሰላማ መተርጉመ መፃሕፍት 13መ/ክ/ዘ
- አባ ሮሜ (አብርሐም) ወደ አማርኛ

1816 አራቱ ወንጌላትን

1821 ሐዲስ ኪዳንን

1832 ሙሉ መጻሕፉን

*አለቃ ተወልደ መድኅን ወደ ትግረኛ

1894 ብሉይ ኪዳንን

1948 ሐዲሰ ኪዳን

የቀጠለ...

- አናሲሞስ ነሲቡ ወደደ ኦሮምኛ

  1893 ብሉይ ኪዳንን

  1899 ሐዲስ ኪዳንን

- በአሁኑ ሰአት በሐገራችን ላይ መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቋንቋዎች እየተተረጎመ ይገኛል

  - ጉራጊኛ
  - በአኝዋክኛ
  - ሲዳሚኛ
  - ወላይትኛ

የቀጠለ...

- ዛሬ በብዛት የሚገኘው 66ቱ 1953
- 81 መጽሐፍ ቅዱስ 1980ዓ.ም በአቡነ ተ/ሃይማኖት ዘመን
- በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ባልተገባ መልኩ የሚዘጋጁ የሰውን ሀሳብ የያዙ መጻህፍታት አሉ ለምሳሌ
- መጽሐፍ ቅዱስ በቀላል አማርኛ
- አዲሲቷ ትርጉም
- ህያው ቃል
- ሐዲስ ኪዳን
- ወንጌል

መጽሐፍ ቅዱስ ከቋንቋ ወደ ቋንቋ እንዴት ይተረጎማል

መጽሐፍ ቅዱስን ለመተርጎም ሁለት ነገሮች ያስፈልጋሉ

፩ ፈሪሃ እግዚአብሔር

፪ የቋንቋ እውቀት

ፈሪሃ እግዚአብሔር የላቸው ሰዎች ከሚያደርጉት መካከል ጥቂቶቹን

- ሮሜ 8፥26‹‹በማየነገር መቃተት ይማልድልናል››

ትክክለኛው‹‹መንፈስ ቅዱስ ስለ መከራችንናስለ ችግራችን ይፈርድልናል››

ሮሜ 8፥34‹‹ስለኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው ››

ትክክለኛው ‹‹የሚፈርድስ ማን ነው የሞተው ይልቁንም ከሙታን ተለይቶ የተነሳው በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው ደግሞ ስለ እኛ የሚፈርደው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ::››

2ቆሮ 5፥20‹‹እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማ  ድ ስለ ክርስቶስ መልዕክተኞች ነን ››

የቀጠለ...

- ምሳ 10፥7‹‹የፃድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው›› ‹ ደግ ሰዎች በደግነታቸው ሲታወሱ ይኖራሉ›

ኢያ 7፥6‹‹እርሱና የእስራኤል ሽማግሌዎች በእግዚአብሔር ታቦት ፊት እስከማታ ድረስ በግንባራቸው ተደፉ ›› ‹እስከ ምሽት ድረስ ተዘርረው በመውደቅ ቆዩ›

መዝ 118፥6‹‹የፃድቅ መታሰብያ ለዘለአለም ይኖራል›› ‹ደግ ሰው ዘውትር ሲታወስ ይኖራል›

የቀጠለ...

- ማቴ 10፥42‹‹ማንም ከእዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ ዋጋው እውነት እላችኋለው አይጠፋም ››
- ት.ዘካ 1፥12-13‹‹የእግዚአብሔርም መልዐክ መልሶ አቤቱ ሁሉን የምትችል ሆይ ሰባ ዘመን የተቆጣህባቸውን የኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች የማትምራቸው እስከ መቼ ነው ››
- ዘፍ 19፥1 ‹‹ሎጥም ባያቸው ጊዜ ሊያነጋግራቸው ከተቀመጠበት ተነስቶ ሔደ ፊቱን ደፍቶ ወደ ምድር ሰገደላቸው››

፪ የቋንቋ እውቀት

- 2ቆሮ 5፥20‹‹ስለ ክርስቶስ መልእክተኞች ነን››
- መዝ 86፥1‹‹መሰለቶቿ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው››

ትርጓሜ ለምን አስፈለገ

1. የሚጋጩ የሚመስሉ ቃላትን ለማስታረቅ

   ማቴ20፥20-21 እና ማር10፥35-37(ዮሐንስና ያዕቅብ)

   መዝ 138፥7 እና ማቴ 18፥20(በመካከላችሁ እገኛለው)

2. የተቋጠረውን ለመፍታት

ት.ዳን 5፥25‹‹ማኔ ቴቄል ፋሬስ››

የቀጠለ...

ማኔ ማለት እግዚአብሔር መንግስትህን መዘናት ማለት ነው

ቴቄል ማለት የተመዘነች መንግስትህ ቀላ ተገኘች ማለት ነው

ፋሬስ ማለት መንግስትህ ለሌሎች ተሰጠች ማለት ነው

3. ከኃጥያት በፊት ብሩህ የነበረው የሰው አዕምሮ ስለጨለመ ትርጓሜ አስፈልጓል

4. የዘመናት ልዩነት ስላለ

+2ጴጥ 1፥20፣ሐዋ 8፥31፣ሉቃ24፥27

የትርጓሜ የአይነቶች

1. ነጠላ ትርጓሜ
2. ምሥጢራዊ ትርጓሜ
3. ምሳሌያዊ ትርጓሜ
4. አንድምታዊ ትርጓሜ

1. ነጠላ ትርጓሜ

- ነጠላ ትርጓሜ የሚባለው ንባቡን ወስዶ ያለምንም ሀተታ የሚረጉም የትርጓሜ ስልት ሲሆን በተጨማሪም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቀጥታ ወስደን ብንጠቀምባቸው ከስህተት ጎዳና የማይጥሉንን ያካትታል
- ለምሳሌ፡-ዘፍ 1፥1 ‹‹በመጀመርያ እግዚአብሔር…››
- ማቴ 26፥41‹‹ወደ ፈተና እንዳትገቡ…››
- መዝ 118፥164‹‹ስለ ፅድቅ ፍርድ በቀን 7 ጊዜ..››
- ኢያ 24፥15‹‹የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ…››
- መዝ51፥9‹‹አድርገህልኛልና ለዘለአለም …››

2. ምሥጢራዊ ትርጓሜ

- ይህ አይነቱ ትርጓሜ ንባቡን ሳይከተል ምሥጢሩን ብቻ ጠብቆ የሚተረጉም ነው።
- 1ቆሮ 2፥7‹‹ተሰውሮ የነበረውን የእግዚአብሔርን ጥበብ በምሥጢር እንናገራለን ››
- ለማሳሌ፡- ኢሳ 9፥2‹‹በጨለማ የሄደ ህዝብ ብርሃንን አየ በሞት ጥላ ውስጥ ለሚኖሩ ብርሃን ወጣላቸው
- መክ11፥1‹‹እንጀራህን በውኃ ላይ ጣለው ከብዙ ቀንም በኋላ ታገኘዋለህ››(ሉቃ 14፥13-14 ግብዣ ባደረክ ጊዜ ድሆችንና ጉንድሾችን ፣አንካሶችንም ጥራ የሚመላሱልህ ብድራት የላቸውምና ብፁእ ትሆናለህ በጻድቃንም ትንሳኤ የመልስልሀልና)

የቀጠለ...

- ማቴ 27፥46‹‹አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ››

1. ለአብነት ማቴ11፥29
2. ለአቅርቦተ ሰይጣን
3. ትንቢቱን ለመፈጸም መዝ 21፥1

ማር 10፥18‹‹ቸር መምህር ሆይ ..ስለምን ቸር ትለኛለህ ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር የለም››

ሉቃ11፥27‹‹የተሸከመችህ ማህፀን የጠባሀቸው ጡቶች ብፁአን ናቸው››

የቀጠለ

- ማር10፥25‹‹ባለጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ የቀላል››
- ሙክ 7፥16‹‹እጅግም ፃድቅ አትሁን እጅግም ጠቢብ አትሁን››
- ማቴ 5፥29‹‹ቀኝ አይንህ ብታሰናክልህ ..››

3 ምሳሌያዊ ትርጓሜ

- ምሳሌያዊ ትርጓሜ አንድን ነገር የበለጠ ግልጽ ለማድረግ በምሳሌ ይነገራል በዚህ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተምር ነበር
- ማር 4፥34‹‹መስማት በሚችሉ መጠን እነዚህን በሚመስል በብዙ ምሳሌ ቃሉን ይነግራቸው ነበርያለ ምሳሌ ግን አልነገራቸውም ለብቻቸውም ሲሆኑ ነገሩን ይፈታላቸው ነበር››

የቀጠለ...

- ት.ኢሳ 5፥1-2
- መኃ 4፥12‹‹እህቴ ሙሽራዬ የተቆለፈች ገነት የተዘጋች ምንጭ የታተመም ፈሳሽ ናት››
- ዮሐ 2፥19 -21‹‹ይህንን ቤተመቅደስ አፍርሱት ከብዙ ቀንም በኋላ አነሳዋለው .... እርሱ ግን ሰውነቱን ቤተ መቅደስ ይል ነበረ››
- ማቴ 27፥23‹‹እረኛ በጎቹን ከፍየሎቹ እንደሚለይ እርስ በእርሳቸው ይለያቸዋል በጎችን በቀኙ ፍየሎችን በግራው ያቆማቸዋል

የፃድቃን በበግ መመሰል

- በግ ትሁት ነው አንገቱን ዝቅ አድርጎ ወደ ታች እያየ ይሄዳል
- በጎች እረኛቸውን ያውቃሉ ድምፁንም ይሰማሉ ይከተሉታል
- በግ ሀፍረቷን በላቷ ትሸፍናለች
- በግ ጭቃ አትፀየፍም
- ፃድቃንም ትሁታን ናቸው እተሞታቸውን እያሰቡ ይኖራሉ
- ፃድቃንም የሚያምኑትን አምላክ ያውቁታል ትእዛዙን ይጠብቃሉ
- ፃድቃንም የራሳቸውን ኃጢአት በንስሐ የወንድማቸውን በትዕግስት
- በሐይማኖታቸው

የኃጥአን በፍየል መመሰል

- ፍየል ትዕቢተኛ ነች ሽቅብ እያየች ትሄዳለች
- ፍየል ሃፍረቷን በላቷ አትሸፍንም
- ፍየል ጭቃ ትፀየፋለች

- ፍየል በሄደችበት ሰው ማሳ ውስጥ እየገባች ሰውን ታሳዝናለች

- ኃጥአንም ትዕቢተኞች ናቸው እለተ ሞታቸውን አያስቡምና
- የራሳቸውን ኃጢአት በንስሐ የወንድማቸውን በትዕግስት አይሸፍኑመምና
- በሃይማኖታቸው የሚመጣባቸውን ይፀየፋሉና
- ኃጢያትን እያደረጉ አምላካቸውን ሲያሳዝኑ ይኖራሉና

የቀጠለ...

- ት.ዳን 2፥34‹‹እጅ ሳይነካው ድንጋይ ከተራራ ላይ ተፈንቃሎ ከብረትና ከሸክላ የሆነውን የምስሉን እግሮች ሲመታ ሲፈጭ አየሁ ››

- ት.ኢሳ 2፥2‹‹በዘመኑ ፍጻሞ የእግዚአብሔር ተራራ በተራሮች እራስ ፀንቶ ይኖራል››

4 አንድምታ ትርጓሜ

- አንድን ታይለ ቃል አንድ ጊዜ ከተረሳሙ በኋላ አንድም ይህንን የመሰለ ሌላ ተጨማሪ ምክንያት አለ እያለ 10 ና 15 ጊዜ ድረስ የሚወርድ የትርጓሜ ስልት ነው። ለምሳሌ
    - ኦርዮን የሞቱን ደብዳቤ እንዴት ይዞ ሄደ፡-
- ማንበብ አይችልም ነበርና
- አንድም በንጉሱና በጦር መሪው ብቻ በሚያውቁት ሲለተጻፈ
- አንድም በንጉስ ማህተም ታትሞ ነበርና
- አንድም ባይጠረጥር ነው እንጂ ቢጠረጥር ገልጦ ባየው

የአንድምታ ትርጓሜ ትምህርት ቤቶች

1. የእስክንድርያ ትርጓሜ ቤት ፡-በ6ዐዓ.ም በቅዱስ ማርቆስ አማካኝነት በግብፅ ተመሰረተ የመጀመርያው ትርጓሜ ትምህርት ቤት ሲሆን የትርጓሜ ስልታቸውም ምሥጢርን እንጂ ንባቡን አይከተሉም
2. የአንፆክያ ትርጓሜ ቤት በነጠላ ትርጓሜ ብቻ ያስተምር ነበረ

ሁለቱም ትርጓሜ ቤቶች በትምህርት ስልታቸው መለያየት ይነቃቀፋሉ

የቀጠለ...

- የአንፃክያዎቹ የእስክንድርያዎችን ሰባልዮሳውያን ይሏቸው ነበረ ፡-
- (ሞደልስቲክ ሞናርኪዝም፣አንዱ ገፅ በተለያዩ ዘመናት ቅርፁን ለዋውጦ ታየ)
- የእስክንድርያዎቹ የአንፃክያዎቹን የጳውሎስ ሳምሳጢን ልጆች ይሏቸዋል
- (ዳይናምስቲክ ሞናርኪዝም፣ቃል አካል ሳይኖረው በአብ አካል ውስጥ የኖረ ኃይል ነው)

የአንድምታ ትርጓሜ በኢትዮጵያ

- ፃድቁ ዮሐንስ ዘመን (1659-1674)
- አድያም ሰገድ ኢያሱ(1674-1698)
    1. የብሉይ ኪዳን መፃህፍት
    2. የሐዲስ ኪዳን መፃህፍት
    3. መጻሕፍተ ሊቃውንት
    4. መፅሐፈ መነኮሳት

የአንድምታ ትርጓሜ በኢትዮጵያ

- 1. የላይ ቤት(1716 በፊት)

+ብዙ ጊዜ የአንድምታ ትርጓሜ ይረዝማል

+የታች ቤትን ትርጓሜ እንደ ማጣቀሻ አይጠቀሙም

- 2. የታች ቤት(1716 ዓ.ም ተመሰረተ)

+በመምህረ ኤስድሮስ ተመሰረተ

+አለቃ ወልደ አብ ከ600 በላይ መፃህፍትን አንብበው አሻሽለውታል በዚህም የትርጓሜ አባት ተብለዋል።

የላይ ቤትና የታች ቤት ንፅፅር

የላይ ቤት

- መልአኩ ገብርኤል በስድስተኛው ወር ተላከ ስለምን በስድስተኛው ወር ተላከ ቢሉ በስድስተኛው ቀን የተፈጠረ ሰው አዳም በድሎ ነበርና እርሱ ለማዳን ወልድ እንደመጣ ለማጠየቅ ነው ።።ስለምን በዚያ ወራት ተላከ ቢሉ በዚያ ወራት የተፈጠረ ፍጥረት በዚያ ወራት በተፈጠረ አዳም በደል ምክንያት ተጎድቶ ነበርና እርሱን ለማዳን ወልድ እንደመጣ ለማጠየቅ ነው።።አንድም በስድስተኛው ሺ ተላከ ።።ጌታ ሰው መሆኑ ስድስተኛው ሺ ሲጀመር ነውና። ስለምን ገብርኤል ተላከ ቢሉ...

የታች ቤት

- ኤልሳቤጥ በፀነሰች በስድስተኛው ወር ገብርኤል የሚባል መልአክ ከእግዚአብሔር ታዞ መጣ ።።ሳድስ ወር ጌታ በስድስተኛው ወር ሰው መሆኑን ያሳያል።።እንኪን በወር በእለት ይመስለዋልና

ቀኖና ቅዱሳት መጻህፍት

- ቀኖና ቃሉ የግሪክ ሲሆን መለኪያ መስፈሪያ ማለት ነው። ቀኖና ቅዱሳን መፃሕፍት ስንል በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቃለው የሚገኙ ቅዱሳት መፃሕፍት ቀኖናያት መፃሕፍት በመባል ይታወቃሉ ይህም ቁጥራቸውንና ይዘታቸው ተሰፍሮ ተቆጥሮ የሚታወቅ ወይንም የተወሰነ ማለት ነው።
- ቀኖና ቅዱሳን መፃሕፍት የብሉይ ኪዳንን እና የሐዲስ ኪዳንን መፃሕፍት ይይዛል ይህም
  - 1ኛ ቀኖና ቅዱሳት መጻሕፍት(prothocanonical)
  - 2ኛ ቀኖና ቁዱሳት መጻህፍት(deuterocanonical)

የቀጠለ...

- 1ኛ ቀኖና ቅዱሳት መጻሕፍት የምንላቸው የብሉይ ኪዳንን መፃሐሕፍት ሲይዝ ያለ ክርክር እና ልዩነት ተቀባይነት ያላቸውን መጻሕፍት ያመለክተናል
- 2ኛ ቀኖና ቁዱሳት መጻህፍት ደግሞ በጥንታውያን አብያተክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው በሌሎቹ ደግሞ ተቀባይነት ያላገኙ አከራካሪ መጻሕፍት ናቸው።
- የመጻሕፍትን ቀኖና ቁጥር ለመወሰን 419ዓ.ም ድረስ 6 ጉባኤዎች ተደርገዋል በተለያየ ዘመን የተነሱ አባቶች ትክክለኛ የሆኑትን ቅዱሳት መጻሕፍት የትኞቹ እንደሆኑ በየዘመናቸው አሳውቀዋል።
-

ስድስቱ ጉባኤዎች

1. ቀኖና ሐዋርያት 85ኛው
2. ጉባኤ ግላስያኖስ
3. ጉባኤ ኤፆ
4. ጉባኤ ቅርጣግና -----393
5. ጉባኤ ሎዶቅያ ------399
6. ጉባኤ ቅርጣግና------419

የመጻህፍትን ቆጥር ካሰውቁ አባቶች

1. ቅ/ቀለሜንጦስ ዘእስክንድርያ ------2መ/ክ/ዘ
2. ቅ/አውሳቢዎስ ዘቂሳርያ ----------340ዓ.ም
3. ቅ/አትናቴዎስ----------367ዓ.ም
4. ቅ/ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም ----------385ዓ.ም
5. ቅ/ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት --------390ዓ.ም
6. ቅ/ዮሐንስ አፈወርቅ----------407ዓ.ም
7. አምፊሊክዮስ ዘኢቆንዮን----------395ዓ.ም

የሥርዓት መፃህፍት

- አብጥሊስ ሲኖዶስ
- ትዕዛዝ ሲኖዶስ
- ግፅው ሲኖዶስ
- ስርዓተ ፅዮን ሲኖዶስ
- ዲድስቅልያ
- መፅሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ
- መፅሐፈ ኪዳን ካልዕ
- መፅሐፈ ቀለሜንጦስ

የብሉይ ኪዳን ቀኖና

- የብሉይ ኪዳን ቀኖና ለመጀመርያ ጊዜ የተዘጋጀው በእዝራ እና በነህምያ ዘመን ነው ::የብሉይ ኪዳንን ቀኖና ማዘጋጀት ያስፈለገበት ምክንያት ሀሰተኞች ነቢያት ህዝቡን እያደናገሩ፣ መጻሕፍት ያላሉትን እንዲህ ተብሏል እያሉ የሀሰት ትምህርትን ይሰጡ ስለነበር እዝራና ነህምያ እነሱ እስከነበሩበት ዘመን ያሉትን መጻህፍት በ3 ክፍል አዘጋጁት እነርሱም፡-
    1. ቶራ፡-የኦሪት መጻሕፍት
    2. ነቢ‌ብ፡- የነቢያት መጻሕፍት
    3. ተቢ‌ብ፡- የታሪክ መጻሕፍት

::

የሐዲስ ኪዳን ቀኖና

- የሐዲስ ኪዳንን ቀኖና ያዘጋጁልን ሐዋርያት ናቸው።ቀኖናውንም ማዘጋጀት ያስፈለገው በ ሁለት ምክንያት ነው

1. አይሁድ በጃምኒያ ጉባኤ አድርገው ለራሳቸው ታልሙድ የሚል መፅሐፍ ስላዘጋጁ።
2. የሀሰት ወንጌሎች ስለበዙ
    1. ሐራጥቃ-------‹የጴጥሮስ ወንጌል›
    2. ኢቦናውያን
    3. ናዝራውያን
    4. ኤልሳቃውያን
    5. ግኖስቲክ---የጴጥሮስ ራዕይ፣የቶማስ ወንጌል

የሐዲስ ኪዳን ቀኖና

- የሐዲስ ኪዳንን ቀኖና ያዘጋጁልን ሐዋርያት ናቸው።ቀኖናውንም ማዘጋጀት ያስፈለገው በ ሁለት ምክንያት ነው

1. አይሁድ በጃምኒያ ጉባኤ አድርገው ለራሳቸው ታልሙድ የሚል መፅሐፍ ስላዘጋጁ።
2. የሀሰት ወንጌሎች ስለበዙ
    1. ሐራጥቃ-------‹የጴጥሮስ ወንጌል›
    2. ኢቦናውያን
    3. ናዝራውያን
    4. ኤልሳቃውያን
    5. ግኖስቲክ---የጴጥሮስ ራዕይ፣የቶማስ ወንጌል

የመፃህፍት ቁጥር ስንት ነው

1. አይሁድ ----------39/24/5
2. ግሪክ ኦርቶዶክስ--------76
3. ካቶሊክ ቤ/ክርስቲያን---73
4. ኦርቶዶክስ ተዋህዶ------81
5. ፕሮቴስታንት----------66

መናፍቃን ከማይቀበሏቸው መፃህፍት መካከል

- መፅሐፈ ኩፋሌ፣ሄኖክ፣ዮዲት፣ተረፈ ኤርሚያስ ፣መ.ባሮክ፣ፀሎተ ምናሴ፣መቃብያን ፣ጦቢት ወዘተ ይገኝበታል
- መፃህፍታቱን ላለመቀበላቸው ምክንያታቸው
- 1. አይሁዳውያን አይቀበሏቸውም ሰባው ሊለቃናት አልተረጎሟቸውም
- 2. እነዚ መፃሕፍት ቢያስፈልጉ ጌታም ሆነ ሐዋርያት ከእነርሱ ጠቅሰው ባስተማሩ ነበር።

የቀጠለ...

- እነዚን መፃህፍት ግን ሰባው ሊቃናት ተርጉመዋቸዋል ሐዋርያትም ጠቅሰው አስተምረዋል ለምሳሌ፡-
- ይሁ 1፥14‹‹እነሆ እግዚአብሔር በሁሉ ላይ ይፈርድ ዘንድ ከአእላፋት ቅዱሳን መላእክት ጋር ይመጣል ኃጥአንም ሁሉስለ ኃጥያታቸው ስራ ሁሉ ከዳተኞችና ኃጥያተኞችም የሚይገባውን ቃል ሁሉ በእርሱ ላይ ስለተናገሩ ይዘልፋቸዋል››
- ሄኖ 1፥9‹‹ፍርድን ያደርግላቸው ዘንድ እነሆ ከቅዱሳን ጋር የመጣል ሽንጉርጉሮችንም ያጠፋቸዋል ኃጥአንና ሽንጉርጉሮችን ፈፅመው በእርሱ ላይ ስላደረጉት ሁሉ ሥጋዊውን ሁሉ ይወቅሳል››

መናፍቃን ካልተቀበሏቸው አንዳንድ ቁም ነገሮች

- ዘፍ 3፥1-5(ሔዋንና እባብ አወሩ)
- ኩፋ 5፥8-17‹‹በዚያ ቀን የእንስሳትና የአራዊት ሁሉ ከዚህ ዓለም የሚመላለሰው ፍጥረትና የወፎች የሚንቀሳቀሰውም ፍጥረት ሁሉ በአንድ አንደበት ከመናገር ተከለከለ››

ዘፍ 4፥17‹‹ቃየንም ሚስቱን አወቃት ፀነሰችም ሔኖህንም ወለደች››

ኩፋ‹‹ሔዋንም ልጇ አዎንን ወለደቻት ....ቃየንም እህቱ አዎንን ሚስት ትሆነው ዘንድ ወሰዳት››

የቀጠለ….

- ዘፍ 6፥1-4
- ሔኖ 9፥16-23‹‹በዚያ ወራት እንዲህ ይሆናል የከበሩ የተመረጡ የሴት የአዳም ሦስተኛ ወንድ ልጅ ከደብረ ቅዱስ ይወርዳሉ ልጆቻቸውም ከቀቃየን ልጆች ጋር አንድ ይሆናሉ››

- ዮሐ 12፥13(ዘንባባ ይዞ ማመስገን)
- ዮ15፥12
- ት.ኤር 39፥15-18፣ተረፈ ኤርሚያስ

- ዮሐ 21፥25‹‹ኢየሱስ ያደረገው ሌላ ብዙ ነገር ደግሞ አለ፣ሁሉ በእያንዳንዱ ቢፃፍ አለም እራሱ ባልበቃቸው ››
- ሐዋ 1፥2-3‹‹ደግሞ አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔር መንግስት ነገር እየነገራቸው በብዙ ማስረጃ ከህማማቱ በኋላ ህያው ሆኖ ለእነርሱ እራሱን አሳያቸው››

መፅሐፍ ቅዱስ እርስ በእርሱ ይጣላልን?

- መፅሐፍ ቅዱስ የተፃፈው በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ነው በመሆኑም ምንም እንኳን በተለያየ ዘመን፣ጊዜ፣ቦታ፣ሰዎች ቢፃፍም የታሪክ መፋለስ የትርጉም መጣረስ የለበትም አስገኚው እግዚአብሔር ነውና።
- በመሆኑም በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚጣረሱ የሚመስሉ ቃላት በትርጓሜ ይታረቃሉ ለአብነት ያህል

የቀጠለ….

- ዘዳ 6፥4‹‹እስራኤል ሆይ ስማ እግዚአብሔር አምላክህ አንድ እግዚአብሔር ነው ።››
- ማቴ28፥19‹‹በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም››
- ዮሐ 10፥30‹‹እኔና አብ አንድ ነን››
- ዮሐ 14፥28‹‹አብ ከእኔ ይበልጣል ››
- መ.ሲራ 2፥18‹‹በሰው እጅ ከምወድቅ በእግዚአብሔር እጅ አንውደቅ››
- ዕብ 10፥31‹‹በህያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው››

የቀጠለ...

- ማቴ27፥5(ታንቆ ሞተ)
- ሐዋ1፥18-19(ሆዱ ተሰንጥቆ አንጀቱ ተዘርግፎ ሞተ)
- 1ሳሙ16፥1-5‹‹እንዴት እሔዳለው ሳኦል ቢሰማ ይገድለኛል....እሰዋ ዘንድ መጣሁ በለው››
- መዝ118፥104‹‹እግዚአብሔር የሀሰትን መንገድ ጠላሁ››
- 2ሳሙ14፥27(4 ልጆች አሉት)
- 2ሳሙ18፥18(ለመጠርያው ሐውልት አቆመ)

ምዕራፍ አራዊልድ ምፅሐፍት

አዋልድ ማለት ምን ማለት ነው

- አዋልድ የሚለው ቃል የብዙ ሲሆን ትርጉሙም ልጆች ማለት ነው።ልጅነታቸው ለመፅሐፍ ቅዱስ ሲሆን በቅርፃቸውም ሆነ በይዘታቸው አስራው ቅዱሳት መፃሕፍትን የሚመስሉ እርሱን የሚተነትኑ ያጠረውን አስረዝመው የረቀቀውን አጉልተው ምሥጢሩን ገልጠው የሚናገሩ ቅዱሳት መፃሕፍት ናቸው ።

የአስራውና የአዋልድ መፃሕፍት ግንኙነት

1. **የአሥራውና አዋልድ መጻሕፍት ግንኙነት**
   1.1. **በዓይነታቸው፡-** አሥራው መጻሕፍትን የሕግ፣ የታሪክ፣ የመዝሙርና የጥበብ፣ የትንቢት ብለን እንደከፈልን ሁሉ አዋልድ መጻሕፍትም በዓይነታቸው በዚሁ ምድብ የሚጠቀሱ መጻሕፍት አሉ።

- ለምሳሌ- የሕግ - ፍትሐነገስት፣ የታሪክ - ተአምረ ማርያም፣ገድለ ሐዋርያት ገድለ ተክለ ሃይማኖት፤ የጥበብና የምስጋና - ውዳሴ ማርያም፣ ሰዓታት፣ አርጋኖን፤ የትንቢት - ፍካሬ ኢየሱስ ወዘተ ይጠቅሳሉ።

   1.2. **በባለቤታቸው፡-** ለሁሉም መጻሕፍት በባለቤትነት የምትይዛቸውና የምትጠቀምባቸው ቅድስት ቤተክርስቲያን ነች፣

   1.3. **በቅድስናቸው፡-** ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የሚፃፉ ናቸው ስለሆነም ቤተክርስቲያን ሁሉንም አረጋግጣ ትቀበላቸዋለች፣

- 2ጢሞ 3፥13‹‹የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መፅሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳፅ ልብንም ለማቅናት በፅድቅም ላለው ህይወት ይጠቅማል››

አዋልድ መፃሕፍት በዘመናት

- በብሉይ ኪዳን
- ሀ. የያሻር መፅሐፍ 2ሳሙ1፥18‹‹ዳዊት ስለሳኦልና ሲለ ልጁ ዮናታን የኃዘን ቅኔን ተቀኘ የይሁዳ ልጆች ያስተምሩ ዘንድ አዘዘ እነሆ ይህ በያሻር መጽሐፍ ተፅፏል››

ሰባው ሊቃናት-------መፅሐፍ ልዩላን

ቩልጌት----------የምርጦች መፅሐፍ

ኢያ 10፥13‹‹ይህ በያሻር መፅሐፍ የተፃፈ አይደለምን››

ለ. የእግዚአብሔር የጦርነት መፅሐፍ 1ነገ 11፥43

ሐ. የእስራኤል ነገስታት ታሪክ መፅሐፍ

1ነገ15፥23፤15፥32 ፤16፥14……

የቀጠለ

- መ. የይሁዳ ነገስታት ታሪክ መፅሐፍ
- ሰ. ሚሽናህ‹‹ዘዳግም››(ረቢ ጃዳድ ሃ ናሲ 2 መቶ ዓ.ም)
- ረ. ገማራ‹‹መደምደምያ››
- ሠ. ዜናሁ ለሙሴ

በዘመነ ወንጌል

- የሐዲስ ኪዳን መፃሕፍት ከአዋልድ መፃሕፍት እየወሰዱ ተናግረዋል ይህ መፅሐፍ ቅዱስ አዋልድ መፃህፍትን እንደሚደግፍና ልንጠቀምባቸው እንደሚያስፈልግ ያሳየናል። ለአብነት...
- 2ጢሞ 3፥8‹‹ኢያኔስና ኢያንበሬስ››
- ማቴ 2፥23 ‹‹በነቢያት ናዝራዊ ይባላል››
- ይሁ ቁ 8(ስለ ሙሴ ሥጋ)
- ሉቃ 10፥29-39(ወንበዴዎች ስለደበደቡት ሰው)

በዘመነ ሐዋርያነ አበው

- በዚህም ዘመን አዋልድ መፃሕፍት ይፃፉ ነበር በሐዋርያት እግር የተተኩ ሐዋርያነ አበው መካከል
- ቀለሜንጦስ ዘሮም
- ፖሊካርፐስ(ለፊልጲስዩስ፣ ለሰርምኔስ)
- አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ
- ፓፒያስ
- ሄርማን (ኖላዊ)

በቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት

- ሰማዕቱ ዮስጢኖስ(በብሉኪዳን ስለጌታችን የተነገረውን እንዴት ፍፃሜ እንዳገነኘ)
- አቴናጎረስ(ማርቆስ ኦሬሌዎስና ኮሞዶስ ለተባሉ የሮም ባለስልጣናት)
- እነ ቅዱስ ቴዎፍሎስ ዘአንፃክያ ፣ቅ/ሄሬኔዎስ.....

በዘመነ ሊቃውንት

- በዘመነ ሊቃውንት እጅግ ብዙ አዋልድ መፃሕፍት ተፅፈዋል። ምክንያቱ

1. ምዕመናን በመብዛታቸው
2. መናፍቃን በመነሳታቸው መልስ ለመስጠት
3. በሰማዕታት ዘመን ያለፉትን ሰማዕታት ለማዘከር
4. በአካል መሔድ ላልቻሉት ቦታ በፅሁፍ ለመድረስ
5. ለተፈጠሩ ክርክሮች ውሳኔ ለመስጠት

የአዋልድ መፅሐፍት አይነቶች

- የአዋልድ መፅሐፍት በአይነታቸው ከ አስር በላይ ናቸው ከእነርሱም

1. መልዕክታት (ቅዱስ አትናቴዎስ ፣ቀ/ዮሐንስ አፈወርቅ..ወ.ዘ.ተ..)
2. ትርጓሜ መፃህፍት
3. ገድላት +አውሳብዮስ -----የሐዋርያትን ገድል
   +አግናጢዮስ -----የፖሊካርፐስን ሰማዕትነት
   +ቅ/አትናቴዎስ ---የአባ እንጦንስን
   +አባ ሄሮኒመስ ---የአባ ጳውሊን

የቀጠለ...

- 4. በሮናፍቃን ላይ የተጻፉ መፃህፍት

  +ቅ/አትናቴዎስ ------በአርዮስ ላይ

  +አባ ጀሮም---------በሄልቪዲየስ ላይ

  +ሔሬኔዎስ ---------በዘሞኑ ለነበሩት

  +ቅ/ዮሐንስ አፈወርቅ--በአርዮሳውያን ላይ

  +ቅ/ቄርሎስ---------በንስጥሮስላይ

የቀጠለ….

5. **መጻሕፍተ መነኮሳት፡-** የመነኮሳት ሥራቸውን ተጋድሎአቸውን ክብራቸውን የሚያስረዱ ሲሆኑ በቁጥር ሦስት ናቸው።

   1ኛ መጽሐፍ ማርይሰሐቅ

   2ኛ መጽሐፍ ፊልክስዩስ እና

   3ኛ መጽሐፍ አረጋዊ መንፈሳዊ ናቸው።

6. **የሕግና የሥርዓት መጻሕፍት፡-** በሕግ የተፈቀዱና የተከለከሉ እና አፈፃፀማቸውን የሚያስረዱ ናቸው። ይኸውም ፍተሐ ነገስት/ፍት መንፈስዊና ፍት ሥጋዊ/፣ ሥርዓተ ቅዳሴ፣ ሥርዓተ ምንኩስና፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ወዘተ

የቀጠለ….

7. **የጸሎት መጻሕፍት፡-** በቤተክርስቲያንም በግልም የሚያገለግሉ ናቸው ለምሳሌ፡- ውዳሴ ማርያም፣ መጽሐፈ ተክለሊል፣ መጽሐፈ ግንዘት፣ መልክዓ መልክ ወዘተ፡
8. **የዜማ መጻሕፍት፡-** በቤተክርስቲያን በሰዓታትና በማኅሌት ለምስጋና የሚያገለግሉ በእነ ቅ/ያሬድና አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የተደረሱ በወንጌል ያለውን ምሥጢር በዜማ እያስማሙ የሚያስተምሩ ናቸው።
ይኸውም፡- ድጓ፣ ጸመድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬ፣ መዋስዕት፣ መጽሐፈ ስዓታት ወዘተ፡

የቀጠለ...

9. **ድርሳናት፡-** ድርሳን ስለ አንድ ነገር የተጻፈ፣ ሐተታ ማለት ነው። ድርሳናት የቅዱሳን መላእክትን ክብርና አማላጅነት፣ ተራዳኢነት ድርሳነ መላእክት ማለትም ድርሳነ ሚካኤል፣ ድርሳነ ገብርኤል፣ ድርሳነ ዑራኤል፤ የሰንበትን ክብርና ልዕልና(ድርሳን ሰንበት)፤ ሊቃውንት በአንዳንድ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የደረሷቸው ለምሳሌ ድርሳን ዘዮሐንስ አፈወርቅ አለያም ጌታችን በመዋዕለ ሥጋዌው በተለያዩ ቦታዎች ለተለያዩ ሰዎች ያደረገው ተአምርና ሕማማን የሚያስረዱ ለምሳሌ ድርሳነ ማኅያዊ፣ መስቀል፣ ብርሃን፣ ኖላዊ ወዘተ:

10. **የቁጥር መጻሕፍት፡-** የዘመን አከፋፈልና አቆጣጠርን፣ የአጽዋማትንና የበዓላትን መዋያ ዕለታት የሚወስኑ ቀመሮችን የያዙ ናቸው። ለምሳሌ፡- አቡሻህር፣ ባሕረ ሐሳብ

የቀጠለ...

11. መልክአ መልካት የእግዚአብሔርን የቅዱሳንን የሰውነት ክፍል እረቂቅና ህያው ያልሆኑትን እያነሳ የሚያመሰግን ነው ለምሳሌ....

መልከዐ ማርያም፣

ኢየሱስ፣

አማኑኤል፣

ዮሐንስ፣

ቁርባን፣

መስቀል ወዘተ....

አዋልድ መፅሐፍት ተጋላጭነት

- ቅሰጣ
- ጥፋት

መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት ስድስት ነገሮች ያስፈልጋሉ

- የእብራውያን ስም አወጣጥ
- የአነጋገር ዘይቤ
- ስዕላዊ አገላለጽ
- እንቆቅልሽ
- ግነት
- ውንድም

- የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም
- የመጀመርያው የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም
- ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ኢትዮጵያ
- መጽሐፍ ቅዱስ ከቋንቋ ወደ ቋንቋ እንዴት ይተረጎማል
- የትርጓሜ የአይነቶች
- ቀኖና ቅዱሳት መጻህፍት
- የብሉይ ኪዳን ቀኖና
- የሐዲስ ኪዳን ቀኖና
- መናፍቃን ካልተቀበሏቸው አንዳንድ ቁም ነገሮች

- አዋልድ ማለት ምን ማለት ነው
- የአሥራውና አዋልድ መጻሕፍት ግንኙነት
- 2ጢሞ 3፥13‹‹የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መፅሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳፅ ልብንም ለማቅናት በፅድቅም ላለው ህይወት ይጠቅማል››
- አዋልድ መፃሕፍት በዘመናት
- የአዋልድ መፅሐፍት አይነቶች
- አዋልድ መፅሐፍት ተጋላጭነት